የባለአክሲዮኖች 12ኛ መደበኛ ጠቅላላ የጉባኤ እና 5ኛ የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድ ሕግ አንቀጽ 366(1)፣ 367 (1) ፣ 370 እና 371(1) እንዲሁም በአክሲዮን ማህበሩ መመስረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 18 መሠረት የደቦ ማይክሮ ፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አክሲዮን ማህበር የባለአክሲዮኖች 12ተኛ መደበኛ እና 5ተኛ የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ታህሳስ 3 ቀን 2019 ዓ.ም ከቀኑ 7:30 ሰዓት እስከ 11:30 ሰዓት በአዲስ አበባ አያ ሆቴል /SAYA Hotel / የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ይካሄዳል:: በመሆኑም የተከበራችሁ ባለአክሲዮኖች ወይም በሕጋዊ ወኪሎቻችሁ አማካኝነት በተጠቀሰዉ ቀን፣ሰዓትና ቦታ በጉባዔው ላይ እንዲሳተፉ የዳይሬክተሮች ቦርድ የአከብሮት ጥሪውን ያቀርባል::

1. አክሲዮን ማህበሩን የሚመለከቱ መረጃዎች

1.1 የማህበሩ ስም፡- ደቦ ማይክሮ ፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አማ

1.2 የማህበሩ ዓይነት፡ በማይክሮ ፋይናንስ ስራ ላይ የተሰማራ አማ

1.3 የአክሲዮን ማህበሩ ዋና መ/ቤት አድራሻ፡ አዲስ አበባ፣ ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 03 የቢሮ ቁጥር 111 ቲኬ ሕንጻ

1.4 የአክሲዮን ማህበሩ ድህረ ገፅ: WWW.debomicrofinance.com

15 የአክሲዮን ማህበሩ የምዝገባ ቁጥር: MT/AA/3/0041241/2010

1.6 የአክሲዮን ማህበሩ የተፈረመ ካፒታል: ብር 300,000,000

1.7 የተከፈለ የማህበሩ ካፒታል: ብር 163,426,000

2. የ12ተኛ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች

1. በቀረቡት የጉባዔ አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ ማጽደቅ፣

2. ኦ.ኦ.ስ የ2025/2026 የሒሳብ ዓመት የዳይሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርት መስማትና ተወያይቶ ማጽደቅ፣

3. ኦ.ኦ.ስ የ2025/2026 የሒሳብ ዓመት የውጭ አዲተሮች ሪፖርት መስማትና ተወያይቶ ማጽደቅ፣

4. ኦ.ኦ.ስ የ2025/2026 ሒሳብ ዓመት የተጣራ ትርፍ አመዳደብና ከፍፍል ላይ መወያየትና መወሰን፣

5. የአክሲዮን ማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ ማካሄድ፣

6.ኦ.ኦ.ስ ለ2026/2027 የሒሳብ አመት የውጭ አዲተር መሾምና ክፍያው ላይ ተወያይቶ ማፅደቅ፣

7. የጉባዔዉን ቃለ-ጉባኤ ማጽደቅ ናቸው::

3. የ5ተኛ የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች

1. በቀረቡት የጉባዔ አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ ማጽደቅ፣

2. የ2025/2026 የሂሳብ ዓመት የተጣራ ትርፍን ያልተከፈለ የተፈረመ ካፒታል ክፍያ በመጠቀም የባለአክሲዮኖችን የአክሲዮን ድርሻ ለማሳደግ በቀረበው ሀሳብ ላይ መወያየትና ማጽደቅ፣

3. ማሻሻያ የተደረገባቸውን የአክሲዮን ማህበሩ የመመስረቻ ጽሑፍ አንቀጾች ላይ ተወያይቶ ማጽደቅ፣

3.1.1 አንቀጽ 5፡ የማህበሩ ካፒታል እና አክሲዮኖች ብዛት

3.1.2 አንቀጽ 6፡ የትርፍ ክፍፍል

3.1.3 አንቀጽ 11፡ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስልጣን

3.1.4 አንቀጽ 21፡ የባለአክሲዮኖች ምዝገባ

3.1.5 አንቀጽ 22፡ የአክሲዮን ዝውውር እና ምዝገባ

ማሳሰቢያ

በጉባኤው ላይ መገኘት የሚችሉ ባለአክሲዮኖች ተወካዮቻቸሁ ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ የተሰጠ የውክልና ሰነድ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ በመያዝ ወይም በንግድ ሕግ አንቀጽ 377 መሠረት ጉባኤው ከመካሄዱ ከሦስት ቀን በፊት በዋና መ/ቤት ቢሮ ቦሌ ቲኬ ሕንጻ 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 111 በአካል በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ በማህበሩ የተዘጋጀውን የውክልና ቅፅ ሞልተው በመፈረም ተወካይ መሾምና ተወካይም የውክልና ማስረጃውን በመያዝ የጉባኤው ተካፋይ በመሆን ድምጽ ለመስጠት የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን:: ሆኖም አንድ ባለአክሲዮን በማህበሩ ጠቅላላ ጉበኤ በማንኛውም ችሎታ መወከል የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ስለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል:: ባለአክስዮኖቹ እና የባለአክሲዮን ተወካይ በጉባዔው ሲገኙ ኢትዮጵያዊነታቸውን የሚያረጋግጥ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት እና የፋይዳ መታወቂያ ዋናውን ከኮፒ ጋር ይዘው መገኘት ይኖርባቸዋል::

የደቦ ማይክሮ ፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አ.ማ